የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት
Federal Democratic Republic of Ethiopia
OFFICE OF THE PRIME MINISTER

ሰኔ 7 ቀን 2016 ዓ.ም
አዲስ አበባ

35ኛ መደበኛ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ስብሰባ ውሳኔዎች

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በዛሬው ዕለት ባካሄደው 35ኛ መደበኛ ስብሰባ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳለፈ።

1. **ምክር ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው የኢትዮጵያ መንገዶች ከባለም አቀፍ የልማት ማህበር ጋር የ3ኛ ዙር የከተሞች የመጠጥ ውሃ አቅርቦት እና ሳኒቴሽን ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል ተጨማሪ ብድር ለማግኘት የተፈረመውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ በቀረበ ረቂቅ አዋጅ ላይ ነው።** በብድር የተገኘው 207,200,000 የአሜሪካ ዶላር ሲሆን የመጠጥ ውሃ አቅርቦት፣ የሳኒቴሽንና ሃይጂን አገልግሎት ተጣባራትን ለማሻሻልና የዘርፉን የማስፈጸም አቅም ለማጠናከር የሚውል ነው። ብድሩ ወለድ የማይታሰብበት፣ 0.75% የአገልግሎት ክፍያ የሚከፈልበት ሆኖ 6 ዓመት የችርታ ጊዜን ጨምሮ በ38 ዓመት ተከፍሎ የሚጠናቀቅ ነው። ምክር ቤቱ ብድሩ ከአሀራችን የብድር አስተዳደር ፖሊሲ ጋር የሚጣጣም መሆኑን በማረጋገጥ ረቂቅ አዋጁ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ በሙሉ ድምጽ ወስኗል።

2. **በሁለተኛ ምክር ቤቱ የተወያየው የንብረት ታክስ ረቂቅ አዋጅ ላይ ነው።** የንብረት ታክስ በከተሞች ነዋሪ በሆነው ሕዝብ መካከል ቀትኖሮ የነበት ክፍተል ለማስፈን፣ የመንግስት አገልግሎቶችን በተሻለ ጥራትና በዘመናዊ ሀዲ ማስረብ ለማስቻል እና የከተማ መሰረተ ልማት ማሻሻያዎችን በቀጣይነት ለመተግበር የሚውለውን የሊንስትመንት ወጪ በንብረት ዋጋ ሚደግ ምክንያት በሚጣል ታክስ አማካኝነት ለመሰብሰብ የሚያስችል ነው። አዋጁ በመላ ሀገሪቱ በሚገኙ ከተሞች ውስጥ ተፈጻሚነት የሚኖረው ሲሆን፣ ከልሎችም ይሆንን አዋጅ መሰረት በማድረግ ከተጨባጭ ሁኔታቸው ጋር በተጣጣመ አኳኋን የየራሳቸውን የንብረት ታክስ ህግ እንዲያወጡ ያስችላል። በዚሁ መሰረት ይህንን ለማስፈጸም የሚረዳ ረቂቅ አዋጅ ተዘጋጅቶ ቀርቧል። ምክር ቤቱም በቀረበው ረቂቅ አዋጅ ላይ ከተወያየ በኋላ ወደ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ በሙሉ ድምጽ ወስኗል።

3. **በ3ኛ ምክር ቤቱ የተወያየው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የፊፀርም እና የካፒታል ማሳደጊያ ዕቅድ ላይ ነው።** የባንኩን የሀብት ጥራት ለማሻሻል እና በአስተማማኝ መልኩ የካፒታል መጠኑን በማሳደግ ለኢኮኖሚው ዕድገት እና ልማት የሚያደርገውን አስተዋጽኦ ዘላቂነት ባለው መልኩ ተጣባራዊ እንዲያደርግ ለማስቻል የሚረዱ የውሳኔ ሃሳቦች ለሚኒስትሮች ምክር ቀርበዋል። እነዘህም የባንኩን አስተዳደራዊ ውጤታማነት ማጎልበት፣ የሂሳብ መግለጫዎቹን ጠንካራና ተቀባይነት ባለው መልኩ እንዲዋቀር ማድረግ እና የባንኩን ካፒታል ለማሳደግ የሚረዳ የመንግሥት የፋይናንስ አቅርቦት ማሻሻል የሚሉ ናቸው። ምክር ቤቱ በማሻሻያ አቅዱ ላይ ተወያቶ ወደቀጣይ ተጣባር እንዲገባ በሙሉ ድምጽ ወስኗል።

4. **ሰላሙ ምክር ቤቱ የተወያየው የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ረቂቅ አዋጅ ላይ ነው።** ባለፉት 16 ዓመታት በስራ ላይ የቆየው አዋጅ ሁሉንም የልማት ተዋናዮች ያሳተፈ የብልጽግና ዕቅድ ተግባራዊ ከማድረግ አኳያ፣ ከዓለም አቀፍ ተሞክሮና መርሆች አንጻር፣ ከሕቻ ግዕከላዊ ባንኮች መልካም ተሞክር፣ከገንዘብ ፖሊሲ ውጤታማነት አንዲሁም በፋይናንስ ራስን ከመቻል አንጻር ክፍተቶች ያሉበት በመሆኑ፣ ባለፉት አመታት በአገር ውስጥም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተከሰቱ በርካታ የኢኮኖሚ፣ የፋይናንስ፣ የቴክኖሎጂና የጂኦ-ፖለቲካ ለውጦች በመኖራቸው፣ የባንኩን ጤናማ የፋይናንስ ሥርዓት የማስፈን፣ ዋጋን የማረጋጋት እና ለኢኮኖሚ ዕድገት አስተዋጽኦ የማድረግ ተልዕኮ ለማሳካት አዋጁን ማሻሻል እንደሚገባ ስለታመነበት ረቂቅ አዋጁ ተዘጋጅቶ ቀርቧል።

ምክር ቤቱም በቀረበው ረቂቅ አዋጅ ላይ ከተወያየ በሁዋላ ጉባኤቶችን ታከለው ወደ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ በሙሉ ድምጽ ወስኗል።

5. **በመቶ፵ሰል ምክር ቤቱ የተወያየው ስለጥንቸ ስራ በቀረበው ረቂቅ አዋጅ ላይ ነው።** ባለፉት አመታት በሀገር አቀፍም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ በርካታ የኢኮኖሚ፣ የቴክኖሎጂ፣ የእደረጃጀትና የአሠራር እና የመንግስት ፖሊሲ ለውጦች በመኖራቸው፣ ሀገራችን ለረጅም ጊዜ ዝግ አድርጋው የነበረውን የጣንክ ስራን ለውጭ ሀገራት ክፍት ማድረጓን ተከትሎ ይህንን ለመምራት፣ የፍታድ አሰጣጥን ለመወሰን እና ለማስተዳደር የሚያስችል የህግ እና የቁጥጥር ስርአት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ረቂቅ አዋጁ ተዘጋጅቶ ቀርቧል። ምክር ቤቱም በቀረበው ረቂቅ አዋጅ ላይ ከተወያየ በኋላ ጉባኤቶችን ታከለውበት ወደ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ በሙሉ ድምጽ ወስኗል።

6. **በመጨረሻም ምክር ቤቱ የተወያየው የአካባቢና ማህበራዊ ተጽዕኖ ግምገማ ረቂቅ አዋጅ ላይ ነው።** የልማት ፕሮጀክቶች ከመተግበራቸው በፊት የአካባቢና ማህበረሰብ ተጽእኖ ግምገማና ጥናት እንዲካሄድባቸው በማድረግ ተጽእኖዎቹን አስቀድሞ በመተንበይ አሉታዊ ተጽእኖዎችን ለማስቀረት ወይም ለመቀነስ መተግበር ስላለባቸው ስራዎች የሚደነግግ እና የአካባቢ ተቢታ ቁጥጥር አሰራርን በተቀናጀ መልኩ ስራ ላይ ለማዋል የሚያስችል ወጥ የሆነ ሀገራዊ የአካባቢና ማህበራዊ ተጽዕና ግምገማ ረቂቅ አዋጅ ተዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቧል። ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ ጉባኤቶችን በማከል ወደ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ በሙሉ ድምጽ ወስኗል።

//